# <u>ለካናዳዋ: ውብ: ከተማ: ቫንኮቨር (Vancouver)</u>

**<u>ከዶክተር: ጥላሁን: ውብ: ዜማዎች</u>**

አቋቋምሽማ፥
ልብ: ያስደነግጣል፥
ፈገግታሽ: ግሩም: ነው፥
ጭራሽ: ነብስ: ያሳጣል ።

ለውበትሽ:ገላጭ:ላድርግና:ውበትሽ:ውስጥ:ሰላም:ዲሞክራሲ:እድገት:ብልጽግና:ብሎም:አንድነት:ለዚያውም:የአለም:ስብስብ:በሞላበት:እያየሁ: ላልተረዳሁት:እስቲ:ልጠይቅሽ: በሞቴ ።

# <u>ውግዘት:ስንት:ዓምት:ይፈጃል ?</u>

እኛ:ኢትዮጲያውያን:ተፈጥሮ:ለግሦን:ኃሮአችን:በሚገኝ:ባዶ:ስፍራ:በቀላሉ:ጫር:ጫር:ተደርጎ:መኖርን:ለምደን:እንደዚሁም:መሪዎቻችን:እንዳንጋፋ:
የጥበብን:መንገድ:እንደየከፋታቸው:ደረጃ:ቆልፈው:በመያዝ:ብዙሃኑ:አሜን:ብሎ:እንዲገዛ:ለማድረግ:በመቻላችቸውና:ጥቂት:አሻፈረኝ:ባይ:የጥበብን:እፍታ:መቅመስ:የቻሉትን:ዳግም:ቢቻል:በተላያየ:መንገድ:የነሱ:ተከታይ:እንዲሆኑ:ማድረግ:ለምሳሌ:በጋብቻ:መጥለፍ፥በስልጣን:መዋለል፥በንዋይ:ብሎም:በመጠኑ:ጥበባቸውን:በተግባር:እንዲያውሉ:መፍቀድ:ካልሆነም:ግለሰቦችን:በዘዴ ማስወገድ ።
ለዚህ:ተግብር:እንደመሳሪያነት:ካገለገሉት:ድርጅቶች:ውስጥ:የሃይማኖት:
ድርጅቶች:ባለፉት:ስርኣቶች:ውስጥ:ያበረከቱት:አስተዋጸኦ:ቀላል:አይደለም።

ይህ:ጽህፍ:ይህንን:ታሪካዊ:ስሕተት:ለመተንተን:ሳይሆን:ዛሬም:ይህ:ታሪካዊ:ስሕተት:እንዲያውም:ከማርጀት:ይልቅ:ጎርምሶና:ፈርጥሞ:እያደቀቀን:ለንፋስ:ዳርጎን:በመላው:ኣለም:ተበትነን:መልሰን:እንኩዋን:እንዳንሰባሰብ:
የውግዘት:ኣውሎንፋስ:በመሃላችን:ሃያ:ኣራት:ሰኣት:እንዲጦዝ:በመደረጉ:ማዶ:ለማዶ:ከመተያየት:በስተቀር:ነጮቹ:እንደሚያደርጉት:ጡዘቱን:ልናጠናው:ኣልደፈርንም:ይህንንም:ስል:በጭራሽ:ኣልተሞከረም:ሳይሆን:ጥናቱን:ወይም:ለመቀራረብ:የሚደረገው:ርብርብ:በተቀራረበ:ጊዜ:ተደጋጋሚ:ሙከራ:ባለመደረጉ:ነውጡ:እንዲፈረጥም:እና:በያለበት:እያረዳን:ለስምምነት:እንዳንበቃ:ኣድርጎናል:እዚህ:ላይ:በሃገራችን:ያለው:የፖለቲካው:ጡዘት:ላለንበት:
ኣዙሪት:የአንበሳውን:ድርሻ:እንደሚወስድ:አልተጠራጠርኩም ።

በኣሁኑሰኣት:የኔ:ትውልድ:ከኮከቡ:ነው:መሰለኝ:በመላው:ኣለም:
ተበትኑዋል።
ታዲያ፤በየደረስንበት:ደስታም፥ሓዘንም፥መራብ፥መጠማት፥መታመም፥ሲብስም፡አልጋላይ፡
መዋል፡ሊደርስ፡የሚችል፡ተፈጥሮኣዊ፡በመሆኑ፡ይደርስብናል፡ደርሶብናልም።

እንደማንኛውም፡የሰው፡ልጅ፡ፍጡር፡እኛም፡እንደባይህላችን፡እንደእምነታችን፡ቀደም፡ብዬ፡ የዘረዘርኳቸውን፡ወይም፡ሌሎች፡የማህበራዊ፡ህይወት፡አጋጣሚዎችንን፡ተረዳድተን፡ የምናሳልፍበት፡ወግ፥ባህል፥ልማድ፥እንዲያው፡በኣጠቃላይ፡መንገድ፡አለን። ለምሳሌ፤በክርስትና፤እምነታችን:ስታመም:አስታማችሁኛል፥ስራአብ:አብልታችሁኛል፥ ስታረዝ:አልብሳችሁኛል፥ስታሰር፡ጠይቃችሁኛል፡

የሚል:ጠያቂ:መንፈሳዊ:ቃል:እንደ:አለ:አውቃለሁ። (አደራ:ፈጽመሃቸዋል!!ብላችሁ:አትጠይቁኝ) ለምን:ቢባል? እኔም:እኮ!!የናንትው:ትውልድ:ነኝ። ጥቂቶችን:አይመለከትም:እንጂ:ብዙዎቻችን:መለያችን:አይመቸኝም፥ስራ: አለኝ፥ችግር:ውስጥ:አትክተተኝ፥ነገ:ተጉዋዥ:ነኝ፤

(መንገደኛነኝ):የሚል:ታርጋ:ስላለን:እኔም:ግብሬን:ገብሬ:ታርጋዬን:ለጥፌአልሁና። ሌላም:አዲስ:ታርጋ:ከወጣ;ሰነበተ:የማን:ዓባል:ነው:ኦሮሞ:ነው፥አማራ:ነው፥ትግሬ:ነው፥ውራጌ: ነው፡ ወዘተ።

መጽሓፉ:ግን:ይህን:አይልም:ታዲያ:ባለፈው:የነጮቹ:ወር:ዲሴምበር: (2012,December) ሕመም :ላይ:የነበረ:አንድ:ወንድማችን:ሕመሙ:ባሰበትና: አልጋ: ላይ: ይውላል፡እኔም :ይህን:ግለሰብ:የማውቀውና:በጉዋደኝነት:አብረን: የነበርን:ነው:ቀደም:በሎ: አፍሪካ:ምድር :በመሆኑ:ሲታመም:ለመጠየቅ:ወደ:መኖሪያ:ቤቱ:ብቅ:አልኩ:እንደሚታወቀው:እዚህ:ሀገር:የነጠላ: ኑሮ:(ብቸኛ):ይበዛልና:እሱም:ብቸኛ:ስለነበረ:ሕመሙ:እየጠናበት:ሲሄድ:አልጋላይ:በዋለበት:ሰኣ ት:እንዲያው:ወንድሜ:ማን:ያግዝሃል:ማንስ:ደፋ:ቀና:ያደርግሃል:ስል:ጠየኩት:እሱም:ከላይ:ከጠቀ ስኳቸው:መንፈስዊ:ቃሎች:ቃሉን:የሚያከብሩ:መንግስት:ከመደበልኝ:አስታማሚ:ውጭ:የሚከባ ከበኝ:እህት:ወንድሞች: አሉኝ:ኣታውቃቸውም፡እንዴ፡አለኝ?እንደማላውቃቸው:ነገርኩት: የምፀልይበት:ቤተክርስቲያን:አባሎች:ናቸው:አለኝና:በፊት:አንተ:ከምትጸልይበት:ቤተክርስቲያን: ውስጥ:ነበሩ:እኮ!! አለኝ:የቤተክርስቲያኑን:ለሁለት:መከፈል:ባውቅም: እነማን:ነበሩ:የሚለውን :በዕርግጥ:ኣላውቅም:አለማወቄን:ገላፅኩለት: በደከመ:አቅሙ:የሰዎቹን :ስም:ጠራልኝ :የማውቀው:ስም:ግን:አልነበረም: ብቻ:የሁሉም:ስም:የኢትዮጲያዊ:ስም:ነው።

በመሃሉም:ታማሚው:ግለሰብ:ሕመሙ:ኣዳከመውና:የሆስፒታል:አልጋ:ላይ: በዋለበት:ሰኣት :እነዚያን:ታማሚ:ወንድማችንን:ተራ:በመግባት:የሚንከባከቡትን:እህትና:ወንድሞች:በኣካል:ለመ ተዋውቅ:ቻልኩኝ። ይህ:በሆነበት:ሰኣት:ግን:ታማሚው:ወንድማችን:በሱ:መታመም፡ምክንያት፡ መተዋወቃችንን :ህመሙ፡አዳከሞት፡ስለ:ነበር:የሚያውቅበት:ደረጃ:ላይ: አልነበረም። አፈር:ነህና:ወደኣፈር:ትመለሳህ:ስለ:ተባለ:ታማሚው:ወንድማችን:አረፈ:በሱ:ህመም:ሳቢያ:የተዋ ወኳቸው:የጸደንያ:ቅድስት:ማሪያም:ቤተክርስቲያን: አባላት:ከወንድማችን: እረፍት:በኃላ :ለሱ:በተደረገው:የኣርባ:ቀን:መታሰቢያ:ላይ:እንድግኝ:ጠሩኝ:ይህ:ቤተክርስቲያን:ከመኖሪያ:ቤቴ:የ ሁለት:ወይም:
የሶስት:ደቂቃ:መንገድ:ላይ:የሚገኝ:ቢሆንም:ትክክለኛ:ሕንፃውን:ኣላውቅም:ነበር:ለማንኛውም:ሌ ሎችን:ጠይቄ:ስፍራውን:በማወቄ:ፌብሩዋሪ (February)17,2013:የቅዳሴ: ስርኣቱ:ካለቀ: በኋላ:ደረስኩኝ:ከዚያም:የጸበል:ጸዲቁ:ስርኣት:ወደ:መገባደጃው:ላይ:ይመስለኛል:የቤተክርስቲያኑ :የሰበካ:ጉባኤ:አባል:የሆኑት:ሰው:አንድ:ጊዜ:ምእመናን:አድምጡኝ:ሲሉ:አዳራሹ:ፀጥታ:ሰፈነበት:

ከዚያም:የወንድማችንን:እረፍት:ምክንያት:በማድረግ:ይህንን: የአርባ:መታሰቢያ: ላዘጋጃሁት:
እህት:ወምድሞች:እንደዚሁም:ወንድማችን:አልጋ:ላይ:በዋለበት:ሰአት:አስፈላጊውን:
ሁሉ:ላደረጋቹሁ:ምእመናን:እንደዚሁም:ሌሎች:ወገኖቻችን:በሙሉ:አባታችን:(የሃይማኖት:መሪ)
ምስጋና:ስለሚያቀርቡ:በፀጥታ:እናዳምጣቸው:ካሉ:በሁዋላ:በመቀጠልም:መጨረሻ:ላይ:ማስታወ
ቂያ:ስለሚኖረን:ከአባታችን:ምስጋና:በኋላ:እናቀርባለን:የሚል:ንግግር፡አድርገው:መድረኩን
:ለሃይማኖት:አባት:ለቀቁ:የሃይማኖት:አባት:የምስጋና:ንግግር:እንዳበቃ:ማስትወቂያው:ቀጠለና:ተ
ናጋሪው:እንደምታውቁት:እኛ:ምን:ጊዜም:ለሰላም:እጃችንን:እንደዘረጋን:ነን:አሁንም:ሳንታክት:ሌ
ሎች:ወንድሞቻችን:ከተቀበሉን:የሰላም:ጥሪ:አድርገናል:ይህንንም:በመገናኛ:ብዙሃን:
ተናግረናል:ኢንተርኔት:(internet):ላይም፤አውለነዋል፤የሚል:ነበር:እኔ:የተነገረውን
:ማስታወቂያ:ቀደም:ብዬ:አልሰማሁትም:ወይም:የተባለውን:ጽሁፍ:አላነበብኩም:ነገር:ግን:
የሰላም:ጥሪ:የሚለው:ቃል:ማረከኝና:ተናጋሪው: ተናግረው:ሲያበቁ:እጄን: አውጥቼ:እንድናገር
:ጠየኩና:ተፈቀደልኝ:ከተናጋሪው:አጠገብ:ቆሜ:እናንተ:ይህን:ካሰባችሁ:እኔም:እኔ:በማመልክበት:
ኖኅተ:ሰማይ:ቅድስት:ማርያም:ቤተ:ክርስቲያት:ተናግሬ:ለሰላም:ሙከራ:አደርጋለሁኝ:ብዬ:ንግግ
ሬን:ሳልጫርስ:አዳራሹ:በሴቶች:እልልታ:በወንዶቹ:ጭብጫባ:ደመቀ:ከዚያም:በስፍራው:የነበሩት:
የሃይማኖት:አባት:መስቀል:ትከሻዬ:ላይ:ጭነው:እባክህን:ወንድሜ:እኛ:ኢትዮጲያውያን:በያለበት:
መሳቂያ:መሳለቅያ:ሆነናልና:ይህንን:ቃልህን:እንዳታጥፍ:እኔም:በፀሎት: አግዝሃለሁ:ሰላም:
እንዲወርድ:አድርግ:አሉኝ። ከዚያ:ወጥቼ:ወደ:ቤቴ:ስጎዝም:ሆነ:ቤቴ:ቁጭ :ብዬ:የማስበው:እዚያ:
አዳራሽውስጥ:የነበረው:ያልተጨበጠ:ተስፋና:ደስታ:እንድዚሁም:ምን:ያህል:ሰላም:እንደራቀንና:
ፍቅር:እንዳጣን:አንድነት:የሚባልው:ነገር:እንኳዋን:ተግባሩ:ቃሉ:እንዳራቀን:ለዚሁም:ማስረጃ:በአ
ንድ:የእምነት:ጥላ:ስር:እንኳን:አንድነት:ማጣታችንን:አዕምሮዬ:እንደ:አዲስ:ነገር:ይጠይቀኝ:ጀምር:
ለራሴ:ለኔው:አዕምሮ:መልስ:መስጠት:ባልችልም:ብቻ:እሞክራለሁ:ያልኩትን:ቃል:እንዴት:አድር
ጌ:እንደምጀምረው:ማውጠንጠን:ተያያዝኩ:ይህንን:ኃሳብ:እያውጠነጠንኩ:ከአንድ:ሦምንት:በላ
ይ:ቆየሁ:በመጨረሻም:እንደምንም:ሀይሌን: አሰባስቤ:ለመጀመሪያ: ብቻዬን:ልሞክረው
:ምክንያቱም:ሌሎችን:ባማክር:ብዙ:የተለያየ፤ሃሳብ:ይቀርባል:ስለዚህ:ሳይጀመር :ያልቃል:
ብዬ:በመስጋት:እስከተወሰነ:ደረጃ:ብቻዬን:ልጀምር:ወሰንኩ:አንዱም:ብቻዬን:ልሞክር:ያነሳሦኝ:
ኖኅተሰማይ:ቅድስት፤ማርያም:ቤተክርስቲያን:ሰበካ:ጉባኤ:የስራ:አስኪያጅ:አባላት:አንብበው
:የሚረዱ:አገናዝበው:የሚፈርዱ:የጥበብን:በር:ያንኳዋኩ: በመሆናቸው:ሰላም: የሚያሰፍኑ:
ናቸው:ብዬ:ስላመንኩ:ብዙ:ደጅ:ጠኚ:ላለማብዛትም:ጭምር:ነበር።

በዚህም:መሰረት:ፌብሩዋሪ(February):መጨረሻልይ:ለኖኅተ:ሰማያት: ቅድስት:ማሪያም
:ቤተክርስትያን:ሰበካጉባኤ:የስራ:አስኪያጅ:አባል:ለሆነው: ለአንድ:ወንድሜ: ደወልኩና:
ከሰላምታ:ልውውጥ:በኁላ:በጸደንያ:ቅድስተ: ማሪያም:ቤተክርስቲያን:ተገኝቼ: የሰማሁትን
:ገልጬለት:እኔም:የኖህተሰማያት:ቅድስት:ማርያም:አባል:በመሆኔ:የኔነት:ተስምቶኝ:የሰላም:ጥሪ
ው:ተግባራዊ:እንዲሆን:የሰጠሁትን:ቃል:ነገርኩት:እሱም:በጣም:ጥሩ:ነው:እንደያውም:እኛ:ቀደም
:ብለን:ይህንን:ጉዳይ:የሚከታተል:አንድ:ኮሚቴ:አቋቁመናል:አለኝ:እኔም:ጥሩ:ነው:
አላወኩም:ነበር:እንዲያውም:ለኔ:ነገሩን:አቀለለልኝ:ማለት:ነው:አልኩት:እሱም:በቃ:ጥሩ:እኔም:ለ
ሌሎች:የስራ:አስኪያጅ:ኣባላት:ነግርና:ሁኔታውን:እናመቻቻለን:አለኝና:በዚሁ:የስልክ:ንግግራችን:
ለእለቱ: ተቋጨ። በበነጋታው:ለጸደንያ: ቅድስት:ማርያም:ቤተክርስትያን:ሰበካጉባኤ:

የስራ:አስኪያጅ:አባል:ደውዬ:በኖኅተሰማይ:ቅድስት:ማርያም:ቤተክርስትያ:በኩል:ጉዳዩ:ቀና:አመ ለካከት:እንዳለውና:ያው:ንግግር:እንዲጀመር:ጠየኩት:መልካም:ነው:እነሱ:ወደ:ሰላም:ከመጡ:እኛ ም:ዝግጁነን:ነገር:ግን:መታወቅ:ያለበት: ስንነጋገር:ጋዜጠኞች:ባሉበት:መሆን:አለበት:ሁለተኛ: እኛ:ስለሁለቱ: ሲኖዶሶች:ጉዳይ:ተነስቶ:በይፋ:መነጋገር:አለብን:ብለን፥እናምለን:ይህ:ካልሆነ :ግን:ለሰላም:ድርድር:አንቀርብም:አለኝ:መጀመሪያውኑ:ጉዳዩን:ለብቻዬ: መያዜን:እራሴን :እንዳልወቅሰው:አድርገኝ:ሳይጀመር:ኣላለቀምና:ለማንኛውም:ጉዳዩን:ከሌሎች:የስራ:አመራር:ዓባ ላት:ጋር:ተነጋግረንበት:ቢቻልም:እኔን:ጥሩኝና:እንነጋገር:ብዬው:በዚሁ:ስልክ:ተዘጋ። ሁኔታው:በጣም:አሳሰበኝ:ለማንም:ሳልናገር:በሁለቱም:በኩል:በስልክ:በየእለቱ:መገናኘት:ጀመርን: በዚሁ:መልክ:ግንኙነታችን:እየቀጠለ:ሲሄድ:በሁለቱም:በኩል:የመነጋገርያ:አጀዳችን:ምንድነው:የ ሚል:ጥያቄ:መቅረቡ:አልቀረም:እኔም:አጀንዳው:ድርድሩ:ሲጀመር:እንደማቅረብ:እየገለጽኩኝ:ማ ርች:(March) 18,2013:ላይ:የጸደኒያ:ቅድስት:ማሪያም:የሃይማኖት:አባት:ድርድሩን: ለመጀመር:ዝግጁ:እንደሆኑ:ገለጹልኝ:በበነጋታው:ስልክ:ደውዬ:ኖኅተሰማይ:ቅድስት:ማሪያም:የ ሥራ:አስኪያጅ:አመራር:አባል:ጋር:በጸደኒያ:ቅድስት:ማሪያም:ስምምነት:መደረሱን :እና: ለመነጋገር:ዝግጁ:መሆናቸውን:ነግሬው:እነሱም: እንዲዘጋጁ:ነገርኩት:እሱም:ከመጀመሪያው :ቀን:ቀዝቀዝ:ባለሁኔታ:የምንነጋገርበት:አጀንዳ:ካለ፥አለኝ:እኔም:ለሁለቱም:ወገኖች:ቀደም :ብዬ:የመጀመሪያው:ቀን:የትውውቅ:መገናኝ:እንደሚሆን:ነግሬአቸው:ስለነበር:ሁለቱም:የተቀበሉ ት:በመሆኑ:በዛሬው: ንግግራችን:ብዙም:በስልክ:መነጋገር:ባልፈልግም: በድጋሚ:የሚያነጋግረን :አጀንዳ:አለወይ:የሚል:ጥያቄ:ስላቀረበልኝ:አዎን:ስል: ለምሳሌ:የሚል:ጥያቄ:ቀረበልኝ:እኔም: ለጊዜውም:ቢሆን:እሱን:ለማስታገስ:ከተለያዩ:ክፍል:ቤ|ክ:በተመለከተ:መግለጫዎች:በመውጣታ ቸው:ምዐመናኑን:ከፋፍለውታል:ይህ:ያነጋግረናል:ስለው:እሱም:እኛ:ለእንደዚህ:አይነት:ነገር:መል ስ:ስልማንስጥ:ችግር:የለብንም:አለኝና:በሌላ:በኩል:ጉዳዩ:በቤ\ክ:የበላይ:አካላት:በኩል:የተዘጋ:ስለ ሆነ:እኛ:ምንም:የምናመጣው:ነገር:ሊኖር:እንደማይችል:የሚል:አስተያየት:ሰጠኝ:በተጨማሪም:ዋ ናው:ነገር:ማንኛውም: ክፍል:ባመነበት:የመጉዋዝ:መብት:መከበር:አለበት:ብሎ:በማያያዝም: ለምሳሌ:ሙስሊም:ወንድሞቻችን:የሚያደርጉት:የመብት:ትግል:ሰላማዊ:ነውየኛም:ሰላማዊ:አመ ጽ:አልባ:መሆን:አለበት:አለኝ:እንዴት:እንደተያያዘ:ባይገባኝም:ለሰላሙ:ላለመቅረብ:ያላቸውን:ስ ሜት:ያንጸባርቃል:በማርች: (March) 13,2013የመሰብሰቢያ: ስፍራ:አገኘሁና:ለሁለቱም: ወገኖች:የመጀመሪያው:የትውውቅ:ስብሰባ:በማርች: (March)23,2013 :ጠዋት:10፥ሰዓት:ላይ: መሆኑን:ነገርኳቸው:ሁለቱም:ወገኖች:ጸደኒያ:በስብሰባው:አጀንዳና:በጋዜጠኞች:መገኘት:ላይ:እያ ንጠረጠሩ:እሺ:ሲሉ:ኖኅተ:ደግሞ:ያነጋገርኩት:ሰው:ቃናው:ጉም:በለበሰ:አነጋገር:ለሌሎቹ: ነግሬ:እሺ:ካሉ:እሺ:አለኝ:እኔ:ግን:በዚህ:ንግግር:ምን:ያህል:ጥላቻ:እመሃላችን :እንደነገሰ: ለማወቅ:ችያለሁ::

ማርች:(March)21,2013ከጸደኒያ:ቤ\ክ:የደረሰኝ:የስልክ:ጥሪ:አስደንጋጭ: ሆነብኝ:ምክንያቱም: ከብዙ:ትዐግስትና:ልምምጥ:በኋላ:የተዘጋጀው:ቀጠሮ:መፍረስ:ለሌላው:ወገን:የምክንያት:መንገድ: ይሆናል:ብዬ:በመስጋቴ:ነበር: ምክንያቱንም:ሲገልጽልኝ:በድርድሩላይ: የሚገኙት:አንዱ: ቤተክርስቲያኑ: አባት:ከሲያትል:(seattle)ስላልመጡ:ነው:አለኝ ።

እኔም:ለኖኅተሰማይ:አባል:ደውዬ:ሁኔታውን:ስነግረው:በነሱም:በኩል:እንዳልተዘጋጁ:ነገረኝ:ልምን:ስለው:ብዙዎች:ስላልተመቻቸው:ሲል:መለሰልኝ:በዚህ:መሰረት:በሁለቱም:በኩል:ወደፊት:ለመምጣት:ውይይቱን:ለመጀመር:የተቸገሩ:ይመስላል።

የበጎቹ:እረኛ:አንዲት:በግ:ብትጠፋበት:የጠፋችውን:በግ:ፍለጋ:ሲማስን:ያድራል:እንጂ:ወደ:ቤቱ:አይመለስም:ይላል:የመጽሃፉ:ቃል:በቃሉም:መሰረት:የጰደኒያ:እና:የኖኅተሰማይ:ቤተክርስቲያን:ዐባላት:በተፈጠረው:ሀገር:አቀፍ:የሃይማኖት:መሪዎች:ከዕምነቱ:ቀኖን:ውጪ:መስራት:መጉዋዝ:በአንድ:የኦርቶዶክስ:ዕምነት:ተከታዮች:መሃከል:መከፋፈልን:የፈጠረውን:ሁኔታ:በውይይት:ለማራቅና:የተበተኑ:በጎችን:የመሰብሰብ:የመጀመሪያ:ቀን:የመገናኛ:መድረክ:ከከሸፈ:በኋላ:ልፋ:ያለው:አንድ:ግንድ:ሊያስር:ይለፋል:መቼም:ነገር:ሁሉ:አሮጌ:ተብሉዋአልና:አሮጌ:ነው:አይሰራም:ካልተባልኩኝ:የቀደምት:አባቶቻችን: እናቶቻችን:ምሳሌያዊ:አነጋገር:ወርቅ:ነው:ታዲያ: እኔም:ስሩ:አንድ:የሆነውን:ከጊዜ:ብኋላ:አንድነቱ:በመላላት:ላይ:ያለውን:እምነታችንን:ላልቶ:እንዳይቀር:ከላይ:በመጠኑም:ቢሆን:ልገልጸው:እንደሞከርኩት:ሰላም:በሚለው:ቃል: በመማረኬ:እኔም:የኦርቶዶክስ:እምነት:ተከታይ:ነኝ:እና:የመጀመሪያው:ቀን:ሙከራ:ባይሳካም:እዚላይ:ሳልቆም:ሙከራዬን:ቀጠልኩኝ።

**<u>ምክር፤ፍለጋ፡-</u>**

ሁኔታው:እየተራዘመና:የሚሰጠው:ሰበብ:በተለይ:ከኖኅተ:ሰማይ:ቅድስት:ማሪያም:ቤተክርስቲያን:በኩል:ተስፋ:አስቆራጭ:እየሆነ:በመምጣቱ:ሌሎች:ቅን:አመለካከት:ያላቸውን:ወገኖች:ማማከር:ጀመርኩኝ:በመጀመሪያው:ላይ:ሁሉም:ያማከርኳቸው:ማለት:ይቻላል:ያበደ:ሰው:ሙከራ:እንደሞከርኩኝ:ነበር:የገለጽልኝ:ምክንያቱንም:ሲነግሩኝ:ይህ:ጉዳይ:በሃይማኖት:ሰዎች:ብቻ:ቢሆን:ኖሮ:መጀመሪያውንም:አይፈጠርም:ነበር:ነገር:ግን:ፖለቲካው:ገብቶበታል:የሃይማኖት:መሪዎቻችን:የሚጸልዩትም:የሚያጸልዩትም:በመመሪያ:ነው:መመሪያውም:ቅዱስ:መጽሐፉ:ሳይሆን:የፖለቲካው:መመሪያ:ነው:ነበር:ያሉኝ።

ቀስ:በቀስ:ሁኔታውን:ሳስረዳቸው:በተለይም:አጀንዳ:ይሆናሉ:ያልኳቸውን:መስቀል:ደመራን፥ጥምቀትን፥ፋሲካን፥እንቁጣጣሽን፥ወዘተ:አብሮ:ማክበር:እንጂ:የውስጥ:የውስጭ: ሲኖዶስ:የሚለውን:ተራራ:ለመድፈር:አይደለም:ስላቸው:እንደዚያ:ከሆነ:ጥሩ:ነው:ቀጥልበት:እኛም:ምክራችንን:እንለግስሀለን አሉኝ:በማገኘው:ምክርም:በመታገዝ:የሰላሙን:ጥረት:ቀጠልኩኝ።

**ጥንስሥ:ላይ:ውሃ:አይጨመርም፡-**
ይህንን:ያሉኝን:የጰደንያ:ቅድስት:ማሪያም:በተክርስቲያን:የሃምማኖት:አባት:ናቸው:ለአባባላቸውም:መነሻ:ምክንያት:የሆነው:ጋዜጠኛ:ካልቀረበ:የውጭና:የውስጥ:ሲኖዶስ:ጉዳይ:ካልተነሳ:የሚለው:ሃሳብ:ለመወያየት:መንገድ:ዘግቷል:ስለዚህ:እነዚህን:ሁልት:የተነሱ:ነጥቦች:እንዳይነሱ:በናንተ:በኩል:እርስዎ:ማድረግ:የሚችሉትን:እንዲያደርጉ:ነው:ስላቸው:የተጠቀሙበት:መግለጫ:በእኚህ:

የሃይማኖት:ዐባት:አባባል: ጥንሥስ:ሳይበስል:ውሃ:መጨመር:ጥንስሡን:እንደሚያበላሽ :ሁሉ:ገና:
ከመጀመሪያው:ጋዜጠኛ:እና:የሲነዶስ:ጉዳይ:በዚህ:አንስተኛ:የወንድማማች:ውይይት:ላይ:ማቅረ
ብ:ውይይቱን:ማኮላሸት:ነው።

ስለዚህ:አንተባቀረብከው:አጀንዳ:ላይ:ብቻ:ተነጋግረን:ስምምነት:ላይ:ስንደርስ:ከግራ:ቀኝ:በሚው
ጣጣ፤ሐይል፤ኮሚቴ፤ተመስርቶ፤የውይይታችንን፥ፍሬ፤ተግባራዊ፤ያደርጋል፤ስለዚህ፤ስጋት፤
አይግባህ፤ነበር፤ያሉኝ። በዕርግጥም፤ከሃይማኖት፤አባት፤የሚጠበቅ፤ቃልና፤ተግባር፤ይህነው፤
ሊመሰገኑ፤የሚገባቸው፤ዐባት፤ናቸው።

**<u>የጾም:ውራት:ነው፡-</u>**

ይህን:ዕረፍት:ነገር:የሰማሁት:የጎተሰማይት:ቅድስት:ማሪያም:ቤተክርስትያን:የስራአስኪያጅ:አባ
ል:ከሆነ:ወንድሜ:ነበር:ከላይ:እንዳልኩት:የመጀመሪያ:ቀን:የመተዋወቂያ:ቀጠሮ:ቢፈርስም:ጉዳዩን
:ግብ:ለማድረስ:በምክርም:እየታገዝኩ:ቀጥያለሁና:በስልክ:ስንነጋገር:ለምን:ውይይቱን:ቶሎ:እንደ
ማይጀምሩ:ስጠይቀው:የሰጠኝ:መልስ:ነው:መጽሃፉ:ግን: ጾማችሑ:የተሟላ:እንዲሆን:ይቅር:
ተባባሉ:እንደሚል:እነሱው:የሃይማኖት:መሪዎችችን:ሲያስተምሩ:ሰምቻለሁ:ታዲያ:ወንድሜ:ያለ
ው:አባባል:ሚዛን:ይደፋልን:ፍርዱን:ለምዕመናን።

**መተው:ነው!!**

እነዚንም:ቃሎች:የጋበዘኝ:ይኼው:ወንድሜ:በእለቱ:በዐንድቀን:ስለውይይቱ:መዘግየት:ስናወጋ:እባ
ክህን:ወንድሜ:የጎተሰምይ:ስራ:አስኪያጅ:ሲሰበሰቡ:ጥራኝና:አቤቱታዬን:ላቅርብ:እኔም:በጉዳዩ
:እየደከምኩ:ነው:ሰለው:ያቀረበልኝ:መፍትሔ:ነው።

እዚህ:ላይ:በስልክ:ከምንነጋገረው:የጎተ:ሥራ:አስኪአጅ:ዓባል:ጋር:ብቻ:ሳይሆን:ለውይይቱ:መሳ
ካት:የተቻላቸውን:እንዲያደርጉ:ሁሉንም:የስራዓሥኪያጅ:ዓባላት:መጠየቄን:መለመኔን:መግለጽ:
ወዳለሁኝ:ታዲያ:ሁሉንም:እባካችሁን:ስብሰባ:ስትቀመጡ:ጥሩኝና:ምንም:እንኩዋን:እንዴት:እንደ
ጀመርኩት: ለያንዳዳቸው:ከመግለጽ:ባልደከምም:ጠብታ:ታህል:ትብብራቸውን:ሳላይ:
ደመናማ:ፈገግታቸው:ዳመናነቱን:ከመጨመር:ሳያልፍ:መንገደኛውም:አባት:መጡ።

**<u>ፀበል፡-</u>**
ሲፈውስ:ሰዎችን:ከኣጋንንት:ሲያስጥል:አይቻለሁኝ:ፀበል:መድሐኒት:መሆኑን:አምናለሁኝ:በተለይ
ም:ከኣምላክ:ውጭ:ለሌላ:ባልተገዙ:የሃይማኖት:ሰዎች:ሲከውን:ማለቴ:ነው:እኔም:እኒህ:መንገደኛ:
አባት:መምጣቸውን: እንደሰማሁ:ላለያየንም:ጋንጩር:ሰላም:ላሳጣንም :ደዌ:እሳቸውም:
የድርሻቸውን:እንዲወጡ:ስልካቸውን:ፈልጌ:በስልክ:በዐካልም:ለፀበል:በሄድኩባቸው:ቀናት:ደቂ

ቃም:እድሜ:ናትና:ስለጉዳዩ:እያነሳሁ:አናግሬኣቸው:ነበር:ዋናው፡ ነገር:በእሺታ:እኔን፡ ናገራቸው፡ በራሱ:ቁምነገር:ነው።

ለማንኛውም:እሳቸው:ያሉኝ:ቅንነት:ያስፈልጋል:ካሉኝ:በኋላ:በፀሎት:አግዝሃለሁ:በርታ:ጉድዩ:ከምእመናን:አይደለም:ችግሩ:ያለው:ከኛ:ከካህናቱ:ነው:ምዕመናኑማ:እኛ:እንደነዳነው:የሚነዳ:በግ:ነው። በመቀጠልም:በኔ:በኩል:ብዙም:ነገሩን:ጠለቅ:ብዬ:አላውቀውም:እንደገባኝ:ከሆነ:ከፊትሕ:የደለበ:መሰናክል:አለ:በርትተህ:ካለፍከው:ካሰብከው:ትደርሳለህ:ግን:መሰናክሉን:የምታልፈው:አይመስለኝም:ብለውኝ:ነበር።

**<u>ሁለቱ:አባቶች፡-</u>**

እነዚህን:ለአምላክ:ያደሩ:አባቶች:እንደማንኛውም:የሃይማኖት:አባቶች:እኛም:የኖኅተሰማይ:ቅድስት:ማርያም:ቤተክርስትያን:ዓባሎች:የምንለግሳቸው:ክብር:ሰማያዊ:እንጂ:ምድራዊ:ዓይነት:አይደለም:ምክንያቱም:የሃይማኖት፡ ዓባቶች:ይህንን:ምድራዊ:ግጭታችንን:አይደለም:ሐጢአት:ሰርተን:ፈጣሪ፡ ከፋብን:ስለእኛ:ምህረት:እንድናገኝ:በመጸለይ:ደህንነትን:እንድናተርፍ:ያደርጋሉና:እኔም:ይህንን:ስለማምን:በኖኅተ:ስራ:አስኪያጅ:በኩል:ለሰላሙ:መንገድ:ፍለጋው:በሩ:የተዘጋ:ስለመሰለኝ:ቀደምም:ብዬ:ዓባቶቼን:ከማስቸገር:ይህ፡ ጉዳይ:በኛው:ይፈታል:ብዬ:ስላመንኩ:ነበር: ወደእነሱ:አቤቱታዬን:ያላቀረብኩት:አሁን:ግን:በእኛ:በዓለማውያን:ስላልሆነ:አባቶች:በተግሳጽም: በምክርም፡ አንተም:ተው:አንተም:ተው:ያባብሉ:ብዬ:እነሱ:ዘንድ:ቀረብኩ:እግዚአብሔር: ይስጣቸው :አቤቱታዬን:በጥሞና:አዳመጡ:ከዚያም:ከሰበካ:ጉባኤው:ሥራ:አስኪያጅ:ጋር: እንመክርበታለን:አሉኝ:በደስታ:ከነፍኩ:እነሱ:ባይኖሩ:እንደሓጢያታችን:ብዛት:አይደለም:ከዓምላክ:ዓለማዊ:ሰው:እስ:በሱ:እንዴት:ይኳኋን:ነበር:ብዬም:አስብኩ:ወቅቱ:የዓብይ:ጾም:ወራት:ስለሆነ: የሃይማኖት:አባቶችን:ብዙ:ማስቸገርም:እየፈራሁ:በዕለት:አንድን:ቀን:ኖኅተሰማይ:ቅድስት:ማርያም:ቤተክርስቲያን:ውስጥ:ከማዕድ:አዳራሽ:ሁለቱ:መሃል:ክፍት:መቀመጫ:አግኝቼ:ኧረ:አባቶቼ:አቤቱታዬን:እንዴት:አደረጋቹሁ:አልኩዋቸው:ከጥቂት:ውይይት:በኋላ:አንደኛው:አባት:በቃ:ጉዳዩን:የጉዳዩ:ባለቤት:ምዕመኑ፡ እንዲፈታው:ለምዕመኑ:እንዲቀርብ:ስራ:አስኪያጆች:ጋር:ተነጋግረን: እንዲፈጸም፡ እናደርጋለን:አሉኝ።

የነበረኝን:ዕፎይታና:ደስታ:መግለጽ:አልችልም:በዚህም:መሠረት:በትዕግስት:ጠበኩኝ:ሆኖም:ግን: አልፎ:አልፎም:ቢሆን:አባቶቹን:እንዴት:ነው:ማለቴ፡ እንድተጠበቀ:ሆኖ:ቀናቶች:እየነጎዱ:ሄዱ: በዚህም:ላይ:ላስታውስ:የምወድው:ምክር:እንዲለግሱኝ:ሰዎችን:ከመጠየቄም:ባሻገር:እዚያው: የኖኅተሰማይ:ዓባል:የሆኑ:ዓባላትንም:ጉዳዩን:ገልጬላቸው:እነሱም:በየጊዜው:በስልክም:ሆነ:በአካል:እንደሁኔታው:የደረስኩበትን:ሁንታ:እየነገርኳቸው:ምክርም፡ እቀበል:ነበር:እንዲያውም :ዓባቶች:ያሉኝን:ለምዕመኑ:ይቀርባል:ምዕመናን፡ ይወስናሉ:የተባለኩትን፡ ስነግራቸው፡ ለሎች: ዓባላትም:እንደሚነግሩ:ዓባቶች፡ የወሰዱት:ዕርምጃ:ትክክለኛ:ስለሆነ፤ተግባራዊ:እንደሚደረግም :ምክንያቱም:የሃይማኖት:ዓባቶች:ቃል:ነውና:በማለት:ለስብሰባ:የሚጠሩበትን:ቀን:ይጠብቁ:ነበር::

**ውግዘት:አለብን፡-**

እኔ:እንደነገርኳቸው:ምዕመናን:ለስብሰባ:የምንጠራበትን:ጊዜ:እየጠበቁ: የዓብይ:ጾም:አለቀ:እኔም:ተስፋ:ሣልቆርጥ:በጾሙ:ወራት:ለምመናኑ:ይቀርባል:ብላችሁኝ:ነበር:ጾም :አለቀ:እንዴት:ነው:እያልኩ:ዓባቶችንም:የሥራ:አስኪያጅ:ዓባላትንም:ባገኘሁት:አጋጣሚ:መወት ወቴ:ሣያቋርጥ:ሜይ:(May)12,2013ከጸሎት:በኋላ:በማዕድ:አዳራሽ:የኖኅተሰማይ:ስራ:አስኪያጅ: ሊቀመበር: ሊያነጋግረኝ:እንደሚፈልግ:እኔም:እሱኑ:ስፈልግ:ተገናኘን:ቦታ:ለብቻችን: የምንቀመጥበት በማጣታችን:በኋላ:ስልክ:ልደውልልህና:በስልክ:እንነጋገራለን:ብሎኝ:በዚሁ: ተለያየን:ማታም፤ደውሎ:ከሰላምታ:ልውውጥ:በኋላ:በቀጥታ:ወደ:ጉዳዩገባን:እኛ:ከነኚህ: ሰዎች:ጋር:ቁጭ:ብለን:አንደራደርም:አለኝ: ለምን:አልኩት:እነሱ:ቀኖና:የጣሱ: ቤተክርስቲያናችንን :ፍርድቤት:ያቆሙ:ስለሆነ:ንግግር:አይሞከርም:በተጨማሪም:እነሱ:የውጭው:ሲኖዶስ:ትክክለኛ: ነው:ስለዐሉ:ልንነጋገር:አንችልም:አለኝ:እኔም:የውጭ:የውስጥ:የሚለው:ጉዳይ:አሁን: አይነሳም: አጀንዳው:የተዘጋጀው:መስቀል:ደመራን:ገና:ፋሲካን:ጥምቀትን:አዲስ:ዓመት:ወዘተ:አብረን:እናከ ብር:ማህበራዊ:ችግሮቻችንን: አብረን:እንፍታ:አላስፈላጊ:መግለጫ:በዓካባቢያችን:እንዳይወጣ: እናድርግ: ነው:አልኩት:እንደ:ድሃ:ጎጆም:ደመራ:በየሥፍራው:አናቁም:ብዬ:ነጥብ: ላማንሣትም: ሞከርኩ:እሱም:በተጨማሪም:በመሃላችን:ውግዘት:ስለአለ: ከነኚህ:ሰዎች:ጋር:አብሮ:መብላት :አብሮ:መጠጣትም:የተከለከለ:ነው:አለኝ:ዱሮ:ሀገር:ቤት:እናቶች:ልቤን:ሰወረኝ:ሲሉ:እሰማ:ነበር: እኔም:እንደዛ:የሆንኩ:መሰለኝ:ብቻ:ስለውግዘቱ:የማውቀው:ነገር:የለም:በሌላው:ጉዳይ:መናገር:እ ችላለሁ:አልኩት:ምክንያቱም:ውግዘት:ማለት:አትሥማሙ:ተነከሳሱ:ሰላም:ለመፍጠር:አትሞክሩ: ማለት:ይሆን:ብዬ:ስለፈራሁ:ነው:እና:አትፍረዱብኝ:ቀደም:ባለው:ጊዜ:እንደተማርኩት:ለጠላት:አ ትግዙ:ለጠላት:ያደረ:ጥቁር:ውሻ:ይወለድ:ብለው:ገዝተው:ሀገር:ስላስተባበሩ:በጥይት:የተጋደሉ:ጳ ጳስ:እንደነበሩ:ምስላቸውንም:ወይም:ማዘከርያ:ሀውልታቸው:ቆሞ:አይቻለሁ:ዛሬ:ደግሞ:ሀውልታ ቸውን:የባቡር:ሀዲድ:ገርስሶታል:የታላቁ:ዕድገታችን:ምልክት:መሆኑ:ነውን?? ለዚው:ነው: እንግዲህ:ግራ:የተጋባሁት:እንደ:እኔ:ግራ:ያልታጋባች:ወገኖቼ:አስረዱኝ:እባካችሁን!!!

**በራችን:ክፍት:ነው፡-**

ሁሉም:ይህን:አባባል:ይጠቀሙበታል:ዛሬም:ሊቀመበሩ:ደገመልኝ:እኛ:ከቤተክርስቲያናችን:ማንን ም:አንከለክልም:አለኝ:እኔም:መከልከልማ:አትችሉም:አልኩት:እንደዚሁም: እስራኤል: እና: ፊልስጤም:አደረጋችሁን:በሰራችሁት: ሥራ:አፍራለሁ:አልኩት:በዚያ:ላይ:አብሮ:መብላት: መጠጣት: የለም :የሚል: አካል:በሩን:እንዴት:እንደሚከፍት:እላውቅም:እዚህ: ላይ: በነሱ: ዓባባል: ጥቂት:ግለሰቦችን:እንጂ:ሁሉንም:አይመለከትም: ይላሉ:ብዙን:በጥቂት: በመቀየር: ዕውነቱ:ይለውጥ:እንደሆነ:አላውቅም:ለዚያውም:በምንሰግድለት:በሰማያዊ:አባት:ቤት።

***ኢትዮጲያዊነት፡-***

ሀገሬ:ምድር:ላይ:ስኖር:”ነትን”ብዙም:ትኩረት:አልሰጠሁትም:አፍሪካ:አንድ:ሀገር:ላይ:ስኖር:እስቲ: ይህንን:”አብዋራ”:አሽተው:ይህ:ሀገርህ:ነው:ይላሉ: የሀገሪቱ:ሰዎች: እንዲያው: ትንሽ: ስትጋጫቻቸው: ያኔነው”ነት”:የሚለው: ትርጉም:የገባኝ:እሷም:”ነት”: የሚለውን:ቃል: ጠንቅቃ:የተረዳች:እህት:ነች: ለዚህ:ሁሉ:መነሻ:ምክንያት:የሆነኝ:በወንድማችን :ዓርባ: ላይ:በጸደንያ:ቅድስት:ማርያም:ቤተክርስቲያን:ተገኝታ:የኢትዬጲያዊነት:ግዴታዋን:ስትወጣ:ያየኋዋት:እህታችን:ያለፈው:ወንድማችን:ታሞ:በነበረበት:ሰዓት:ከሌለው:ወገን: ጋር:ሆና: ስታስታምም:አይቻታለሁ:ብዙም:ትውውቅ:የለንም:ያየኋትም:አንድ: ሁለት:ተብሎ: ለሚቆጠር:ጊዚያት:ነው:ታዲያ:ምን:አስደነቀህ:ልትሉኝ:ትችላሁ:ይህች:እህታችን:በኢትዮጵያ:እስላም:ክርስቲያኑ:ሀገር:ያጋራ:ነው፤ዕምነት የግል:ነው:ብሎ: አምኖ:ተባብሮ: ይኖራል: ለሀገር: ችግርም:ለማህበራዊ:ችግርም:በጋራ:ይቆማል:የሚለውን:ሀገራዊ:አባባል:አስታውሳኝ:ነው: እህታችን: የእስልምና:ዕምነት:ተከታይ:ነች!! ታዲያ:ሰላም፥ፍቅር፥አንድነት:አጥተን: የክርስትና: እምነት:ተከታዮች:የጎሪጥ:ስንተያይ:ኢትዮጲያዊነቷዋ:አሸንፏት:በእምነት:ቤታችን:በቤተክርስቲያን: ተገኝታ:ከወገን:ጋር:መቆሟ:አያረካም:አትሉኝም:: በዚህ:የአንድ:ዕምነት:ተከታዮች: የሆን: ወገኖች:መስማማት:ባጣንበት:ሰአት:ይህች:ኢትዮጵያዊት:በቤተክርስቲያናችን:ተገኝታ:ያሳየችው: ኢትዮጵያዊነት:ስላስደሰተኝ:ጥቂት;ስለአስተምሮቷ:ልጫጭር:ወደድኩኝ።

**በተስፋ:ኑሩ፦**

የሚለው:የመጽሃፍ:ቃል:በተስፋ:እንድንኖር:ይመክራልና:በኖኅተ:ሥራ:አስኪያጆች:በኩል:የማይሆን:መልስ:ባገኝም:ተስፋ:ሣልቆርጥ:ሁለቱን:አባቶች:በኖኅተሰማይ:ቅድስት:ማርያም:የሰበካ:ጉባኤ:ለዓባላት:አይቀርብም:አብረን:አንበላም:አብረን:አንጠጣም:የሚለውን:ውሳኔ:በመቃወም:አቤቱታዬን:በድጋሚ:ለሁለቱ:አባቶች:እናንተ:አባቶች:ፍረዱኝ:ብዬ:ደጅ:ጥናቴን:ቀጠልኩ:አባቶችም: ምንም:እንኳን:ባንድላይ:ሁነው:ላነጋግራቸው:ባልችልም:(ዕድሉ:ስላልተሰጠኝ:ነው):በስልክ:አነጋገርኳቸው:አንዱ:አባት:እግዚአብሄር:ይስጣቸው:እስቲ:እኔና:አንተ:ተገናኝተን:እንነጋገር:ብለው:ቀጠሮ:ሰጡኝ:የሥራ:አስኪያጁ:ኮሚቴው:የነፈገኝን:ቁጭ:ብሎ:መነጋገር:እሳቸው:ጋበዙኝ:ሊመሰገኑ: ይገባቸዋል።

**<u>ባንዲራ:ሲወርድና:ሲሰቅል፦</u>**

ልጅ:ሆኜ:ጠዋት:ሲሰቀል:ማታ:ሲወርድ:በክብር:ቆመን:ክብር:ሰጥተን:ልክ:እንደወታደር:ሥርዐተ: ባንዲራውን:ስንፈጽም:ያተግባር:ያኔ:የወታደር:ብቻ:ይመስለኝ:ነበር:ተግባሩን:ከወታደሩ:ኮርጀን: ብንፈጽምም:በኃላ:ሲገባኝ:ግን:ለካ:ያለ:አስተማሪ:መማር:ኖርዋል:ይህን:ትዝታ:ያመጣብኝ:እላይ:እንደገለጽኩላችሁ:በቀጠሮ:እንድንገናኝና:እንድንነጋገር:ከኖኅተ:ቅድስትሰማይ:አባት: ጋር: ወዳደርግነው :የቀጠሮ:ቦታ:ስሔድ:ሥፍራው:በእለቱ:በደመቀ:በዓል:ተይዞ:ኑሮ: ያየሁት: ትርኢት:ነው።

አርበኞች:በተለያዩ:ተሽከርካሪዎች:ላይ:ሁነው:እንዲሁም:ያልደከሙት:ሰልፍ:ገብተው:የነገውን:ተ
ረካቢዎች:በከፊል:ፊት:ሆነው:በመምራት:በከፊል:ደግሞ:በተረካቢው:ትውልድ:እየተመሩ:ባንዲ
ራቸውን:ተሸከመው:ሲተሙ:ሌላም:ትርኢት:ተጨምሮበት:በትዝታ: አረቄ:ሰክሬ:እነዚህ: ሰዎች:
እነደኛ:አሮጌ:ባንዲራ:አሮጌ:አርበኛ:ታሪክ:ተረት:ተረት:ሀገር:ሀገር:ማለት:ኃላ:ቀርነት:ሣይሉ:አሁን:
የተፈጠረው:በትላንትና:ላይ:ተጉዞ:ነው:እያሉል:የህጻን:ፈገግታ:ዓይነት:እየሰጡ:አጸፋውን:ጭብ
ጨባ:እየተቀበሉ:ያልፋሉ:እኔም:አዕምሮዬ:አሁን:አንተ:እንድትኖር:ያለፈው:መኖር:ነበረበት:አትሥ
ደበው:ባጭሩ:ትላንት:ከሌላ:ዛሬ:የለም:ይህንን:አታውቅም:እያለ:የሚሞግተኝ:እየመሰለኝ:ስልኬ:
ጮኸና:ቀሰቀሰኝ:የእሺታ:ቁልፉን:ተጭኜ:አቤት:አልኩ:ካህኑ:ኑረው: የመኪና:መንገድ :በበዓሉ
:ምክንያት:ስለተዘጋ:መኪናቸውን:በአቅራቢያ:ሥፍራ:አቁመው:እየመጡ:እንደሆነ:ነገሩኝና:ተመል
ሼ:ትዝታ:ወደ:ፈጠረብኝ: ትርዒት:መመልከት:ቀጠልኩ::

ትርዒቱ:ማራኪነው:ባንዲራቸውን:ሲያዩ:የሚያሳዩት:ከበሬታ:ግራ:ቀኝ:የታደሙት:ታዳሚዎች:አ
ስቀናኝ:ለምን:ትቀናለህ:አንተም:ሀገር:እንዲሁ:ነበር:ሲለኝ:አንድ:ጎን:አዕምሮዬ:ሌላኛው:ጎን:አዕም
ሮዬ:አሁንስ:እያለ:ወደምርመራ:ቢሮ:ሲገፈትረኝ:ካህኑ:ደርሰው:ኑሮ:ስልኬ:ሲጮህ:እሺታ:ቁልፉን:
ጭቁን: ለቀቅ:አድርጌ:ሃሎ:ስል:እሳቸው:እያየሁህ:ነው:መጣሁ:አሉኝ:እኔም:ከአዕምሮዬ:ምርመራ
:ጥያቄ:ተገላግዬ:ቁና:ቁና:እየተነፈስኩ:ካህኑጋ:ደረስኩኝ:መስቀል:ተሳልሜ:አዕምሮዬ:ካደረሰብኝ
:ድንጋጤ:ቀስ: በቀስ:መውጣት: ቻልኩ።

ተያይዘንም:ቡና:መሸጫው:መደበር:ውስጥ:ገባን:የሥራ:አስኪያጅ:ኮሚቴው:የሰጠውን:ውሳኔ:እኔ
ም:እጋራለሁ:አሉኝ:ካህኑ:ድንጋጤዬ:ሳይታወቅብኝ: ላለመደንገጥ:ሙከራ:እያደረኩ: እንዴት:
አልኳቸው:አየህ:እነሱ:ግራ:ቀኙን: አይታው:ነው:እዚህ:ውሳኔ:ላይ:የደረሱት:ማለትም: ነገሩ
:ወዴት:እየመራ: እደሆነ:ተረድተው:ነው።

በመሰረቱ:እኔ:የተሰደዱትን:ጳጳስ:አልቀበላቸውም:ጳጳስ:አይሰደዱም:ከተሰደዱ:ደግሞ:ሲኖዶስ:ማ
ቋቋም:አልነበረባቸውም:አርፈው:መቀመጥ:ነበረባቸው:ብለው:ጀመሩልኝ:እኔም:አሁን:ጥያቄው:
እሱ:ሳይሆን:እዚህ:ባለንበት:ክልል:ላይ:ነው:ከዚህ:በፊትም:ተናግሬአለሁኝ:ወደዚያ:ከመድረሳችን
:በፊት:እዚህ:የምንኖር:ምዕመናን:አንድ:እስኩዌር:ኪሎ:ሜትር:በማይሞላ:ሥፍራ:ውስጥ:ብዙዎቻ
ችን:አብረን:እንኖራለን:የአንድ:ኦርቶዶክስ:ዕምነት:ተከታዮች:የሆነው:ግን:ተከፋፍለናል:ተራርቀና
ል:ያንን:እናስወግድ:ነው:ጥያቄው: አልኳቸው:አስከትዬም:ወደ:ተራራው:ጥያቄ:አንሂድ:
አልኳቸው: እሳቸውም:ያም:ቢሆን:ውግዘት:አለ:በማሃላችን:አይሞከርም:አሉኝ: አከታትለውም
:ብዙ:የመጽሀፍ:ቅዱስ:ጥቅስን:ጠቀሱልኝ:እንደገባኝ:እኔን:ለማሳመን:የተደረገ:ነው:ብዬ:ገምታለሁ:
ከእኒህ:አባት:ጋር:ህጻን:ልጃቸውን:ተሸከመው:መጥተው:ከሁለት:ሰዐት:ተኩል:በላይ:አወጋን:ግን:
ለውጥ:የለም:እሳቸውም:ያው:እንደሌሎቹ:ቋንቋቸው:አንድ:ነው:ከብዙ:የመጽሃፍ:ቅድስ:ጥቅስ:በ
ስተቀር:እሳቸውም:የተለየ:ማስታወሻዬን:ላይ:አዲስ:ሐሳብ:ወይም:አባታዊ:ምክርም:ሆነ:ሰላም:
የሚያወርድ:ቃል:አልተውሉኝም:ያሉትን:ቃል:በቃል:ላስፍር:ብል:አንባቢውን:ማሰልቸት:ይሆንብ
ኛልና:እዚህ:ላይ:ላቁምና:ሌላኛው:አባት:ደግሞ:ባጭሩም:ቢሆን:በስልክ:ያሉኝን:ሳልነግራችሁ:
ላልፍ:ነበር:ግን:እነሆ:አስታወስኩኝ:ውግዘት:አብሮ:መብላት:መጠጣትን:አይከለክልም:ይህንን:ያ
ሉኝ:ያው:የኖኅተ:ሰማይ:ቅድስት:ምርያም:ሌላኛው:አባት:ናቸው:ውግዘቱ:በዕርግጥ:ካህናት:

አብሮ:መቀደስን:ይከለክላል:የሰበካ:ጉባኤው:እንዴት:ለሰላም:አልቀርብም:እንዳለ:አላውቅም:እኔን :አላማከሩኝም:ግን:ጥቂት:ግለሰቦች:እንዳሻቸው:እያሽከረከሩን:ነው:እኔም:ምንም:ሥልጣን:የለኝ ም:በተሰጠው:ውሳኔ: አዝናለው:አሉኝ:ከእኚህም:አባት:ጋር:ብዙ:ሰዓት:አውግተናል: ጠቅለል: ሲል:ከላይ:ያለውን:ይመስላል።

ምዕመናን:እንዲሁም:ሰላም:ወዳድ:ኢትዮጲያውያን:የአብርሃም:በግ:ለእግዚአብሔር:መስዋዕትነት :የቀረበው:ወይም:የተመረጠው:በራሱ:በፈጣሪ:ፍላጎትና:ትእዛዝ:ነው:እኛስ:የቄሶቹ:በጎች:መስዋዕ ት:የምሆነው:ለማንና:በማን:ትዕዛዝ:ነው።

ይህንን:ያሰኘኝ:የዕርቀ:ሰላሙን:ሁኔታ:የኖኅተሰማይ:ቅድስት:ማሪያም:ቤተክርስቲያን:የሃይማኖት :አባቶች:እራሱ:ባለቤቱ:ምዕመናኑ:እንዲፈታው:ለምዕመናኑ:እንዲቀርብ:እናደርጋለን:ብለው:አንደ ኛው:አባት:ሲነግሩኝ:እኔ:ሁለት:አባቶች:መሃከል:ቁጭ:ብዬ:ሌላኛውም:አባት:እያዳመጡ: ነበር: ነገር:ግን: በኋላ:ላይ:አድማጭ:የነበሩት:አባት:ታዲያ:የዚያን:ሰኣት:ለምዕመናን:ይቀርባል :ሲባል: እንደማይቀርብ:ለምን:አልተቃወሙም:እዚያው:ከጽላቱ:ስር:ቁጭ: ብለን:ባለንበት: ሰዓት: ስላቸው: የሰጡኝ:መልስ:እኔ:አይደለሁም:ያንን:ቃል: የተናገርኩት:የሚል:ነገር:ብቻ: ነበር:ለካንስ :እሳቸው:ጊዜ:መግዣ:ሰዓት:እንጂ:የሚያደርጉትን:አሳምረው:ያውቁ:ኖሮዋል:አጅሬ:ፖለትካ:እዚህ ጋ:ይሆን:ስራውን:የስራው!!እባካችሁየተጠበባቹ:አስተምሩኝ:ይህ:ካልሆነ:በፈጣሪ:ቤት :እንዲህ: ዓይነት:መካካድ:አለውይ??

በዕውነቱ:ተጓዥ:አባት:ብዬ:የጠራኃቸውና:መጨረሻው:ምዕራፍ:ላይ:ያነሳኃቸው:አባት:ጥፋቱ:ከ ምዕመናኑ:ሳይሆን:ከኛው:የሓይማኖት:መሪዎች:ነው:ያሉት:ዕውነት:ነው።ምዕመናን:እንዲያው :እስከመቼ:ነው:እንዴት:ለምን:መቼ:ግልጽ:ይሁን:ለውይይት፤ይቀረብ፤የሚደረገውን: የምታደርጉትን ፤እንወቅ፤የማንል??

ምክንያቱም:ለአንድንት:ለሰላም:በግንባር:ቀደምትነት:መቆም፤የሚገባቸው፤አባቶች: ሊለያዩን :ከቆሙ:ዝም:ብለን:የምናይ:ከሆነ:እነሱ:ምንም:ጥፋት:የለባቸውም።እንዲሁም :የመረጥናቸው :የሰበካ:ጉባኤ:ስራ:አስኪያጅ:አባላትም:ሆኑ:ተባባሪዎች:የሚያደርጉትን:እንቅስቃሴ:ካላወቅን:ጥፋ ቱ:እኛው:የቄሶቹ:በጎች:ላይ:ነው።

ይህንን:ጉዳይ:ትንሽ:ቅርንጫፍ:መዘን:እነሱን:ማለትም:ሰላም:አያስፈልግም:የሚሉንን:ወግነን:ለመ ከራከር:ከሞከርን:ሰብተን:ሞከተናል:ከማለት:ውጭ:ምን:ይባላል:እንደዚሁም:የሚያጃጅል:ሙገሳ: ለማግኘት:እሱማ:እሷማ:ጨዋ:ነው:ነች:የእግዚአብሄርን:መንገድ:ተከትሎ:ተከትላ:አይናገር:አትናገ ር:ዝም: ብሎ:ብላ:አሜን:ብቻ:ለመባል:ከሆነ:በዕርግጥ:የአምላክን:ትዕዛዝ: ፈጽመናልን? አቤቱታ:አቤቱታዬ:በኖህተሰማይ:እኛው:በመረጥናቸው:የሰበካ:የስራአስኪያጅ:አባላት:እንደዚሁ ም: የሃይማኖት:አባቶች:ጭምር:ሰላም:እናውርድ:ጥያቄዬ:በካልቾ:ተመቶ:ተሰብሮአል:ስለዚህ: የኖህተሰማይ:ቤተክርስቲያን:አባላት:(ምዕመናን) ስብራቱን:ጠግናችሁ:ሰላም:እንዲሰፍን: እንደዚሁም:ተቃቅፈን” ጽድቅን:እንድንወርስ:ታደርጉ:ዘንድ:እማጠናለሁ።

ይህንን፡የችግር፡ወቅት፡መርቶ፡ዳር፡የሚያወጣን፡ሙሴ፡እንዲሰጠን፡የሰማይ፡አባት፡ሆይ፡ራራልን፡ብለን ፡እንጸልይ።

አሜን፤አሜን፤

መኮንን፥ ከ ቫንኩቨር (Vancouver )